ብራይተርግሪን

አጭር የፖሊሲ መግለጫ ቁጥር 3

# የአየር ንብረት፣ የምግብ ዋስትና እና ዕድገት

## የኢትዮጵያ የከብት ኃብት ልማትና የተጋፈጠው ውስብስብ ፈተና

በአፍሪካ ቀንድ የምትገኘውና ወደብ አልባ የሆነችው ኢትዮጵያ በበርካታ ነገሮች ስሟ ቢነሳም እንደ ማክዶናልድስ ያሉ የፈጣን ምግብ ቤቶች አገር በመሆን ግን ፈጽሞውኑ የምትታወቅ አይደለችም፡፡ እንዲያውም እንደነዚህ ዓይነቱ ዓለምዓቀፍ ዕውቅና ያላቸው ፈጣን ምግብ ቤቶች በአገሪቷ ውስጥ ገና መንቀሳቀስ አልጀመሩም፡፡ ሥጋቸው ለምግብነት የሚውሉት አብዛኞዎቹ የቤት እንስሳት ዕርባታ የሚካሄደው አነስተኛ አቅም ባላቸው ገበሬዎች ወይም አርብቶ አደሮች ሲሆን ንግድ ተኮር የሆነ ዘመናዊ የእንስሳት ዕርባታ በአገሪቷ ገና አልተጀመረም፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአማካይ አንድ ኢትዮጵያዊ በዓመት 8.3 ኪሎግራም ወይም 18 ፓውንድ ሥጋ ይመገባል፤ ይህም አንድ አሜሪካዊ በዓመት ከሚመገበው አንድ አሥረኛ ማለት ነው፡፡

ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ ግን በከብት ሃብቷ ከአፍሪካ የቀዳሚነቱን ሥፍራ ይዛ የምትገኝ አገር ስትሆን በከብት ኃብት ምርትና ወደ ውጪ በመላክ በአህጉሩ ከሚገኙት አገሮች የበላይነቱን ሥፍራ ይዛ ትገኛለች፡፡ በ2000/2001[*] ዓም የነበረው መረጃ እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ ውስጥ 49 ሚሊዮን ከብቶች፣ ወደ 50 ሚሊዮን የሚጠጉ በጎችና ፍየሎች እንዲሁም 35 ሚሊዮን ዶሮዎች ነበሯት፡፡ በወቅቱ በአገሪቷ ውስጥ በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የኅብረተሰብ ክፍል ቁጥር እየጨመረ ከመምጣቱ አኳያ የአገር ውስጥ የእንስሳት ተዋጽዖ ምርቶች ፍላጎት እያደገ ቢሆንም የከብት ኃብት ልማቱን የማበረታታት፣ የማስፋፋትና የማጠናከር ከፍተኛውን ሚና የሚጫወተው አገሪቷ በውጪ ገበያው መስክ ያላት መጠነ ሰፊ ዕድል ነው፡፡



### የልማት ተግዳሮት የሆነው የአየር ንብረት ለውጥ

እንደ አብዛኞዎቹ የአፍሪካና የመካከለኛ ምስራቅ አገሮች 85 ሚሊዮን ከሚሆነውና በወጣትነት ዕድሜ ክልል ከሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግማሽ ያህሉ ዕድሜው 14ዓመት ወይም ከዚያ በታች ነው፡፡ ይህም የኅብረተሰብ ክፍል በየዓመቱ የ3 ነጥብ ተሩብ ዕድገት በመቶ እያስመዘገበ የሚሄድ ሲሆን ይህም አገሪቱን በዓለማችን ፈጣን የሕዝብ ዕድገት እያስመዘገቡ ካሉት አገሮች መካከል አንዷ ያደርጋታል፡፡ ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ በ2042/2043 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 150 እስከ 170 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቷ የልማት ፍላጎት መጠነሰፊ ቢሆንም ከሕዝቧ 40 በመቶ የሚሆነው መናጢ ደሃ ከሚባለው የሚመደብ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለአብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ተገቢውን የትምህርት ሽፋን ከመስጠት፣ የጤና እንክብካቤ ከማድረግና ንጹሕ ውሃን ከማቅረብ እንዲሁም እያንዳንዱ ዜጋ በአማካይ

[*] በተለየ ካልተገለጸ በስተቀር በዚህ ጽሁፍ ውስጥም ሆነ ከታች በግራፉ ላይ የተቀሱት ቀናትና ዓመቶች በሙሉ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ናቸው፡፡

በሕይወት የሚኖርበት ዘመን ከፍ ከማድረግ አኳያ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ኪሣራ የተመዘገበባት አገር ነች፡፡ በትምህርቱ ዘርፍ ለአካለመጠን ከደረሰው የኅብረተሰብ ክፍል 2/3ኛ የሚሆነው መሃይም ሲሆን ዕድሜያቸው አምስትና ከዚያ በታች ከሆኑት ህጻናት መካከል 38በመቶው የሰውነት ክብደታቸው ከሚጠበቀው መጠን በታች ወይም በሌላ አነጋገር ሰውነታቸው የመነመነ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከ80በመቶ በላይ ከሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተፈጥሮ ላይ በጽኑ ጥገኛ የሆነ የገጠር ነዋሪ ሲሆን በርካታ ኢትዮጵያውያን ለም መሬት ለማግኘት እንዲሁም ለከብቶቻቸው የግጦሽ መስክና በቂ ውሃ ለማግኘት ሽሚያ ውስጥ ሲገቡ ይታያሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት የዓለም ሙቀት መጨመር ከምንግዜውም በበለጠ እውን እየሆነ መጥቷል፡፡ እየተከሰተ ያለው ከፍተኛ የሙቀት መጠን እንዲሁም ሳያቋርጥ እየተከሰተ ያለው ድርቅ የኢትዮጵያ ገበሬ ራስ ምታት፣ ጭንቀትና ስቃይ ሆኗል፡፡ በተለይም 2000ዓም በተወሰነ መልኩ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ ወቅቱን ጠብቆ የሚጥለው ዝናብ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ባለመዝነቡ አገሪቱ በድርቅ ተመትታ ነበር፡፡ በዚህም ድርቅ ምክንያት በሺዎች የሚቆጠሩ ከብቶች ሲሞቱ መጠነሰፊ የሆነ የሰው ዕልቂት እንዳይከሰት ማድረግ የተቻለው የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ዕርዳታ ማግኘት በመቻሉ ነበር፡፡ በዚህ በያዝነው 2003ዓም እንዲሁ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች የአፍሪካ ቀንድ አገራትን አስከፊ የሆነ ድርቅ እያጠቃቸው ሲሆን አሰቃቂው ድርቅ ከተከሰተ ከ25 ዓመታት በኋላም ዛሬም እንዲሁ የምግብ ዋስትናን በአገሪቱ ተግባራዊ ማድረግ ትልቅ ተግዳሮት ሆኖ ይገኛል፡፡

**የግብርና ኢኮኖሚና ግብርና ተኮር ንግድ (አግሮ ቢዝነስ)**

በተደጋጋሚ ሲነገር እንደሚሰማው ግብርና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ነው፡፡ አገሪቱ ወደውጪ ከምትልከው ምርት 60 በመቶ ያህሉን የሚያካትተው የግብርና ምርት ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ግማሽ ያህሉን የሚሸፍን ነው፡፡ እነዚህም ለውጪ ንግድ የሚቀርቡ ምርቶች የቁም ከብትን ጨምሮ ቡና፣ እንደ ባቄላ ያሉ ጥራጥሬዎች፣ የሸንኮራ አገዳ ዝቃጭ (ሞላሰስ)፣ የቅባት እህሎችና ጥጥን ያካተተ ነው፡፡ ከ95 በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ገበሬ ኑሮው ከእጅ ወደአፍ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የእርሻ ተግባራትን ለማከናወን ከመስኖ ይልቅ ዝናብ ላይ ጥገኛ በመሆኑ ሦስት ሩብ እጅ የሚሆኑት ከብቶች የሚረቡት የሰብል ማምረትንና የቁም ከብትን ማርባት በጣምራነት በሚያከናውኑ አነስተኛ አቅም ባላቸው ገበሬዎች ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት፣ የግል ባለሃብቶችና አንዳንድ የልማት ተቋማት ለውጪ ገበያ የሚቀርበውን ምርት ለማበረታታት ሲሉ የከብት ኃብት ልማቱ ዘርፍ ኢንዱስትሪያዊ ዕድገት እንዲሳያሳይ ይመኛሉ፡፡ በ1999/2000 የበጀት ዓመት ኢትዮጵያ 38ሺህ ሜትሪክ ቶን እንቁላል እንዲሁም 48ሺህ ሜትሪክ ቶን የዶሮ ሥጋ አምርታለች፡፡ መጠናቸው ከ2500 እስከ 50ሺህ ዶሮዎችን የመያዝ አቅም ያላቸው ቁጥራቸው በትንሹ እስከ 20 የሚደርስ ዘመናዊ የዶሮ እርባታ ተቋማት በአገሪቷ ውስጥ ይገኛሉ፡፡


በአሁኑ ጊዜ ካሉት የቁም ከብት ማምረቻዎች ሁሉ የቀዳሚነቱን ሥፍራ የሚይዘው ኤልፎራ አግሮቢዝነስ የተሰኘው ድርጅት ሲሆን በአገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የግጦሽ መስክ፣ የሥጋ እና የእንቁላል ዶሮዎች ማርቢያዎች፣ የእህል ወፍጮ ቤቶችን፣ የከብት ማደለቢያና ማረጃ ቦታዎች ያሉት ሲሆን ምርቱንም በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ሱፐርማርኬቶች፣ ሆቴሎችና አየር መንገዶች እንዲሁም ለውጭ ገበያ በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡ ድርጅቱ በአሜሪካ አገር ከሚገኘው «ላንድ ኦሊክስ» ከተሰኘው ታላቅ የወተት ተዋጽዖ አምራች ኩባንያ እንዲሁም ከአሜሪካ ዓለምአቀፍ የተራድዖ ድርጅት ጋር በመሆን በ1997/1998 ዓም ከፍተኛ ምርት መሥጠት ስለሚችሉ የተዳቀሉ

ከብቶች ከማስተዋወቅ ጀምሮ በጉዳዩ ላይ ሥልጠና እስከመስጠት ደርሶ ነበር፡፡ ከ1990 እስከ 2000ዓም ባሉት አስር ዓመታት የኢትዮጵያ የከብት ብዛት በ39 ነጥብ 37በመቶ ያደገ ሲሆን የበጎች ቁጥር በ86 ነጥብ ሦስት በመቶ እንዲሁም የፍየሎች ቁጥር በ109 ነጥብ ሁለት በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡

## የምግብ ዋስትና ተግባራዊነት ተደናቅፎ ይሆን?

በኢትዮጵያ የከብት ልማት ክፍለ ኢኮኖሚ በኢንዱስትሪ ደረጃ እየተስፋፋ መሄድ በአገሪቷ የምግብ ዋስትና ላይ የራሱ የሆነ ዘላቂ ተጽዕኖ አለው፡፡ በኢትዮጵያ ያሉ አብዛኞዎቹ ከብቶች እንዲሁም በጎችና ፍየሎች በመኖነት የሚቀርብላቸው የግጦሽ ሣር ወይም ፉርሽካ ቢሆንም የዶሮና የእንቁላልምርትእየጨመረሲሄድ አብላጫነት ያለው እህል የሚመደበው ለሰዎች ፍጆታነት ሳይሆን ለእንስሳት ይሆናል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የምግብና እርሻ ድርጅት (ፋኦ) ባደረገው ጥናት መሠረት ከ1985 እስከ 1995 በነበሩት ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ለአንድ ከብት የሚመደበው መኖ 4 በመቶ መጨመሩን ገምቷል፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ የሚመረተው ስንዴና የስንዴ ገለባ፣ ማሽላና በቆሎ ለከብት መኖነት እንዲውል እየተደረገ ከሄደ የእነዚህ ሰብሎችን ዋጋ እያሻቀበ መሄዱ የማይቀር ሃቅ ነው፡፡ ይህም እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ በአማካይ ዘወትር የሚመገበውን እንዳያገኝ እንቅፋት እንደሚፈጥር እሙን ነው፡፡




በመጪዎቹ ዓመታት ኢትዮጵያ ወሳኝ በሆነ ምርጫ ውስጥ እንደምትገባ ሁኔታዎች ይጠቁማሉ፡፡ እነዚህም ምርጫዎች አንዱ ያላትን የውሃና የመሬት ሃብት በመጠቀም ለሕዝቧ ፍጆታ የሚውል እህል ማምረት ወይም ሁለተኛው በየጣቢያው ለሚደልቡ ከብቶችና ለሚረቡ ዶሮዎች መኖ የሚሆን እህል ማምረት፡፡ ሆኖም ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ለእንስሳት የሚሆን መኖ ከውጪ ባታስገባም በማደግ ላይ የሚገኘው የሥጋ፣ የወተትና የእንቁላል ንግድ የአሜሪካ የሰብል ጉባዔ የተባለውን ኩባንያ ጨምሮ በርካታ ትርፍ እንደሚያስገኝ የተረዱ ሌሎች የውጪ ነጋዴዎችን ቀልብ እየሳበ ይገኛል፡፡

## የሃብት አጠቃቀም ማነቆ

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ያለው የመሬት፣ የውሃ እና የደን ሃብት በአገሪቷ ውስጥ የሚመረተውን ሰብልና የከብት እርባታ ለመደገፍ በከፍተኛ ጫና ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህም እንግዲህ ገና እንስሳትን እንደ ፋብሪካ ምርት በሰፊው ማርባት ሳይጀመር መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በበረሃማና ከፊል በረሃማ ቦታዎች የሚገኙ፣ ንብረታቸው በጣም ውሱን የሆኑና የእርሻ ዘዴያቸው በአያሌው በዝናብ ላይ ጥገኛ የሆኑ ገበሬዎች ከሚያረቧቸው ከብቶች ጋር እነርሱም እየተከሰተ ላለው የአየር ንብረት ለውጥ የተጋለጡ ናቸው፡፡ በቅርቡ ዓለምአቀፉ የምግብ ፖሊሲ ጥናት ተቋም ባደረገው ጥናት መሠረት በኢትዮጵያ የሚገኙ ገበሬዎች ከዓለም ሙቀት መጨመር ሁኔታ ጋር እንዳይላመዱ እያደረጋቸው ያለው ዋንኛ እንቅፋት የበቂ መሬት እጦት መሆኑን ዘግቧል፡፡

በኢትዮጵያ ካለው መሬት ውስጥ ለእርሻ ተስማሚ የሆነውና ለሰብል ምርት መዋል የሚችለው 10.7 በመቶ ብቻ ነው፡፡ በዓለም ላይ ካሉ የአፈር መሸርሸር ከሚደርስባቸው አገራት ኢትዮጵያ ከቀዳሚዎቹ ቁጥር የምትመደብ ስትሆን በየዓመቱም 2 ቢሊዮን ሜትሪክ ቶን አፈር ታጣለች፡፡ በ1990ዎቹ አጋማሽ በኢትዮጵያ ውስጥ በደን የተሸፈነው መሬት 2.7 በመቶ ብቻ ሲሆን ይህም በ1950ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ከተገመተው የ40 በመቶ የደን ሽፋን ከፍተኛ መቀነስ አስመዝግቧል፡፡

## የፖሊሲ አስተያየቶች

ከሁሉ በፊት የሚነሳው ጥያቄ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ያለውን የዓለም ሙቀት በጽናት ተቋቁሞ ወደፊት ሊከሰት የሚችል የረሃብ አደጋን የሚያስቀርና ዘላቂነት ያለው ተመጣጣኝ የግብርና ምጣኔሃብት ኢትዮጵያ መፍጠር ትችላለች ወይ የሚለው ነው፡፡ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሕዝቡ የምግብ ፍጆታነት የሚውል፤ የወቅቱንና የወደፊቱን ልዩ ልዩ የአልሚ ምግቦች ፍላጎት በመሟላት ረገድ ቅድሚያ በመስጠት ዘላቂነት ያለውና የወቅቱን ሥነምህዳር ግምት ውስጥ ያስገባ የረጅም ጊዜ ዕቅድ መንደፍ አለበት፡፡ መንግሥት ከሲቪል ማኅበረሰቡና ከለጋሽ ድርጅቶች እንዲሁም ከዓለምአቀፋዊ መያዶች ጋር በመተባበር አትክልቶችን፣ ፍራፍሬዎችን፣ ጥራጥሬዎችን እና ሌሎች እህሎችን በአገር ውስጥ የማምረትን ብቃት የሚያሳድግ አጠቃላይ ዕቅድ መንደፍ አለበት፡፡

መንግሥት አገሪቱ በከብት ልማት ላይ ያላትን ከፍተኛ ጥገኝነትና በዘርፉ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም እንዲሁም ከስነምግባር፣ ከምጣኔሃብትና ከሥነምህዳሩ አኳያ ባለው የሃብት አደላደል ላይና ከዚህ ሁሉ ባሻገር ደግሞ የከብቶችን መኖ ከውጪ ማስመጣት ከሚኖረው ተጽዕኖ አንጻር ፖሊሲውን እንደገና ሊፈትሽ ይገባዋል፡፡ ስለሆነም መንግሥት የምግብ ዋስትናን፣ የመኖሪያ አካባቢን፣ አኗኗርን እና ፍትሐዊነትን በመጉዳት የከብት ሃብት በኢንዱስትሪ ደረጃ እንዲያድግ የሚያበረታታ ይፋ የሆነም ያልሆነም ፖሊሲን ማራመዱን ማቆም ይኖርበታል፡፡ የአየር ንብረት ለውጡ የከፋ ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት መንግሥት፣ ለጋሽ አጋሮችና የሲቪል ማኅበረሰቡ የሁኔታዎችን አጣዳፊነት ግምት ውስጥ በማስገባት በገጠር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የከብት ክምችቱን የሚቀንስበትን ሁኔታ ተግባራዊ እንዲያደርግ እንዲሁም የሃብት ክምችቱን በከብት ላይ ከሚያደርግ ይልቅ በሌላ መልኩ እንዲያደርግ መፍትሔ በመፈለግ ስምምነት ላይ መድረስ የሚቻልበትን መንገድ መቀየስ አለባቸው፡፡ መንግሥት፣ ለጋሽ ተቋማትና የሲቪል ማኅበረሰቡ መጠነ ሰፊ የሆነ የሥነ ምህዳር ተሃድሶ ፕሮጀክቶችን በትብብር ተግባራዊ በማድረግ ከሚገባው በላይ የታረሱትንና ለግጦሽ የዋሉትን መሬቶች በማደስ የምግብ ሰብል ምርትን ለማስፋፋት እንዲሁም በዓለም ዙሪያ የሙቀት መጠን እንዳይጨምር በጽናት የሚከላከሉና ዘላቂነት ያለው የዝናብ መጠን እንዲዘንብ ማድረግ የሚችሉ ዛፎችና ሌሎች ዕፅዋቶች እንደገና እንዲበቅሉ በማድረግ በኩል ሊተባበሩ ይገባቸዋል፡፡■

*የፎቶውን ባለቤት አንድሩው ሔቨንስ ነው፡፡*

*የዚህ አጭር የፖሊሲ አስተያየት መሠረት ያደረገው ‹‹ብራይተር ግሪን›› የተባለው ድርጅት የአየር ንብረት፣ የምግብ ዋስትና እና ዕድገት በሚል ርዕስ ኢትዮጵያ ከከብት ሃብት ልማት ጋር የተያያዘችውን ፍጥጫ መሠረት በማድረግ በሚያ ማክዶናልድና ጀስቲን ሲሞን ከተጻፈው የተወሰደ ሲሆን ይህም የብራይተር ግሪን የምግብ ፖሊሲና ተመጣጣኝ ፕሮግራም አንዱ ክፍል ነው፡፡ በብራዚል፣ በቻይና፣ እና በሕንድ የአየር ንብረት ለውጥን እንዲሁም እንስሳትን ለኢንዱስትሪያዊ ምርት አገልግሎት መጠቀምን በተመለከተ በተከታታይ የተጻፈ ተጨማሪ የፖሊሲ ዘገባ እንዲሁም አጭር ጥናታዊ ፊልም በብራይተርግሪን ድረገጽ (www.brightergreen.org) ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡*

Copyright © 2011 Brighter Green
www.brightergreen.org || info@brightergreen.org || 165 Court Street, #171, Brooklyn, NY, USA 11201